# በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የተሿሚ እንደራሴዎች (Appointed Representative) ሚና

## 1. መግቢያ

ተሿሚ እንደራሴ ከካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች አንዱ ሲሆን ይሄው በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 980/2016 ተመልክቶ ይገኛል። መመሪያው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች አይነት፣ የፈቃድ አሰጣጥ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ የያዘ እና እንደ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላዎች፣ ጠባቂዎች እና የኢንቨስትመንት ባንኮች ከመሰሉ ድርጅቶች በተጨማሪ በግለሰብ ደረጃ ፈቃድ ለሚሰጣቸው ተሿሚ እንደራሴዎች ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

የተሿሚ እንደራሴዎች ሠራተኛ ብቻ አይደሉም፤ ለእያንዳንዱ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ የክዋኔ እና የሥነ-ምግባር ዋና ተዋናይ ሆነው የሚያገለግሉ በግለሰብ ደረጃ ፈቃድ ያላቸው ባለሙያዎች ናቸው። ተሿሚ እንደራሴዎች ግብይቶችን የሚፈጽሙ፣ ትንታኔ የሚያካሂዱ እና የህግ ተገዢነትን የሚያረጋግጡ የገበያው ተዋናይ ናቸው። ይህ ጽሑፍ የተሿሚ እንደራሴዎችን የፈቃድ መስፈርቶች፣ የተፈቀዱ ተግባራት እንዲሁም በካፒታል ገበያ ያላቸውን ሚና ይተነትናል። በጽሁፉ የተሿሚ እንደራሴዎች የፈቃድ አሰጣጥ ሂደት፣ መብት እና ግዴታዎች፣ ሊከተሉት የሚገባቸው ጥብቅ የሥነ ምግባር ደንብ ይዳስሳል።

> *"ተሿሚ እንደራሴ ማለት በባለሥልጣኑ የንግድ ፈቃድ የተሰጠውን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ በመወከል ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት የሚያከናውን ሰው ነው።"*

## 2. ተሿሚ እንደራሴዎች

ተሿሚ እንደራሴ ማለት በባለሥልጣኑ የንግድ ፈቃድ የተሰጠውን የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ በመወከል ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተግባራት የሚያከናውን ሰው ነው።

ከሌሎች የካፒታል ገበያ አገልግሎቶች ዋና ዋና ልዩነቶች የሚከተሉት ናቸው፦

- የግለሰብ ፈቃድ፡ ከሌሎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ዘርፎች በተለየ መልኩ ለተሿሚ እንደራሴ በግለሰብ ደረጃ ፈቃድ የሚሰጥ ሲሆን(አንቀጽ 120) ፈቃዳቸው ምንም እንኳን ፈቃድ ባላቸው ሌሎች የካፒታል ገበያ የአገልግሎት ሰጪነት ዘርፎች መታገዝ/ስፖንሰር/ መደረግ የሚገባው ነው።
- የግል ተጠያቂነት፡ ተሿሚ እንደራሴዎች ለድርጊቶቻቸው የግለሰብ ተጠያቂነት አለባቸው። በመመሪያው አንቀጽ 34 እንደተደነገገው አጋዥ/ስፖንሰር/ አድራጊው ለተሿሚ እንደራሴው ድርጊቶቹ ተጠያቂ ቢሆንም፣ ተሿሚ እንደራሴዎች እራሳቸው ከድርጅቱ ሁኔታ ውጭ በሥነ ምግባር ጉድለት ምክንያት የግል ፈቃዳቸው ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።
- አጋዥ/ስፖንሰር/ግዴታ፦ አንድ ግለሰብ የተሿሚ እንደራሴ ፈቃድ ለማግኘት በራሱ ማመልከት አይችልም። ማመልከት የሚችለው ፈቃድ ባለው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ በኩል ወይም ለፈቃድ በሚያመለክት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ በኩል በመታገዝ/ስፖንሰር/ በመደረግ መሆን አለበት (አንቀጽ 120(2))።

ይህ በግለሰቡ እና በስፖንሰር አድራጊው ኩባንያ መካከል የተጠያቂነት ትስስር ይፈጥራል።

በተጨማሪ ከካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ጋር የሚሰራ ሆኖ በመመሪያው ታሳቢ ያልተደረገ ማንኛውም ሰው ባለሥልጣኑ ሊያዘው እንደሚችል በመመሪያው ተመልክቷል።በተለይ ከደንበኛዎች ጋር የሚገናኝ፣ የደንበኛ ንብረቶችን የሚቆጣጠር፣የሚያተዳድር፣ የሚገበያይ፣ የቅሬታዎችን አፈታትን የሚያስተዳድር ወይም በሂደቱ የሚሳተፍ፣ በአደጋ አስተዳደር እና ተገዢነት ውስጥ የተሳተፈ ማንኛውም ግለሰብ እንደ ተሿሚ እንደራሴ ፈቃድ እንዲሰጠው ባለስልጣኑ ሊጠይቅ እንደሚችል በተጨማሪ ያብራራል (አንቀጽ 120(3))።

## 3. ተሿሚ እንደራሴ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች

በመመሪያው ክፍል አስራ ስድስት ውስጥ የተዘረዘረው የተሿሚ እንደራሴ የፈቃድ አሰጣጥ ሂደት፣ ብቃት ያላቸው እና በሥነ ምግባር የተካኑ ግለሰቦች ብቻ ወደ ገበያው እንዲገቡ የሚያረጋግጥ ጠንካራ ማጣሪያ እንዲሆን የተነደፈ ነው።

ሀ) **ብቁነት እና ስፖንሰርነት** (**አንቀጽ** 120 **እና** 121): ብቁ ለመሆን፣ አንድ ግለሰብ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

- አመልካቾች በመመሪያው (በሰንጠረዥ ሁለት) ውስጥ የተገለጹትን ዝቅተኛ የብቃት፣ የልምድ እና የክህሎት ተገቢ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። እነዚህ እንደየ ስፖንሰር አድራጊው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ የሚለያዩ ሆነው ለተሿሚ እንደራሴነት አመልካቹ አስፈላጊው የትምህርት ዝግጅት፣ የስራ ልምድ እና የካፒታል ገበያ ጋር በተያያዘ ስልጠና እና ሰርተፊኬት ያለው መሆን አለበት፣
- በመመሪያው አንቀጽ 16 ስር ያሉትን ሁሉንም የብቁ እና ተገቢነት መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው። እነዚህ በተለይ ከመልካም ስም ጋር የተገናኙ ሲሆኑ ለተሿሚ እንደራሴነት አመልካቹ ከእምነት ማጉደል፣ ስርቆት፣ ፋይናንስ ነክ ወንጀሎች ጋር በተያያዘ ወንጀለኛ ተብለው የማያውቁ፣ ኪሳራ ገጥሟቸው የማያውቁ እና በመልካም ስም የሚታወቅ መሆን አለበት፣
- በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች /መታገዝ/ስፖንሰር መደረግ፤ ማመልከቻው በስፖንሰር አድራጊው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ በመታገዝ የሚቀርብ ሲሆን የሚከተሉትን ጨምሮ አጠቃላይ ሰነዶች መቅረብ አለባቸው፡-
  - የሹመት ወይም የቅጥር ደብዳቤ፤
  - የእጩው የስራ ልምድ ዝግጅት መግለጫ፤
  - የትምህርት ማስረጃ እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ፤
  - ከወንጀል ነጻ መሆኑን የሚያሳይ የምስክር ወረቀት፤
  - እጩው የስነ-ምግባር ደንቡን ለማክበር ቃል መግባቱን የሚያሳይ ማስረጃ፤
  - ከተሿሚ እንደራሴዎች እርምጃዎች የሚነሱ ተጠያቂነቶችን ለመካስ ከስፖንሰር አድራጊው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ለደንበኞች የሚሰጥ ዋስትና፤
  - ፈቃድ ለማውጣት የሚጠየቅ ገንዘብ ክፍያ ማረጋገጫ።

ለ) **የፈቃድ ፈተና መውሰድ እና ማለፍ** (**አንቀጽ** 121(2)):

ሂደቱ እውቀትን እና ስነ-ምግባር የሚገመግሙ ሶስት ወሳኝ ፈተናዎችን ያካትታል፡-

1. **የሙያ ብቃት፣** ለተሿሚ እንደራሴነት እጩው በመመሪያው እንደተገለጸው ወይም በየጊዜው በባለስልጣኑ በሚገለጸው መሰረት ከእንግሊዙ በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ስልጣና ከሚሰጠው ድርጅት “Chartered Institute for Securities and Investments” ደረጃ ሶስት ወይም ተመጣጣኝ ስልጠና ወስደው ፈተና ማለፋቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት።
2. **የፈቃድ ፈተና፣** እጩው በባለስልጣኑ የሚሰጠውን ልዩ የፈቃድ ፈተና መውሰድ እና ማለፍ አለበት።
3. **ቃለ መጠይቅ፣** እጩው በባለስልጣኑ ወይም በተወሰነ አካል የሚካሄድ ቃለ መጠይቅ ማድረግ አለበት።

ይህ ባለብዙ ደረጃ የፈቃድ አሰጣጥ እና ማጣራት ሂደት እጩ ተሿሚ እንደራሴዎች በአካዳሚክ ብቃት ብቻ ሳይሆን ለተግባራቸው የሚያስፈልገውን ተግባራዊ ግንዛቤ እና ሙያዊ ባህሪ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጣል።

4. **የብቃት ማዕቀፍ**

የተሿሚ እንደራሴዎች የብቃት ማዕቀፍ በመመሪያው በሠንጠረዥ ሁለት ውስጥ ተመልክቶ ይገኛል። ይህ ማዕቀፍ ከአጠቃላይ ብቃቶች ባሻገር በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ውስጥ ለእያንዳንዱ ቁልፍ ሚና የሚፈለጉትን የእውቀት፣ የልምድ እና የክህሎት ትክክለኛ መስፈርቶች ያካትታል።

## 5. የተሿሚ እንደራሴዎች ቁልፍ ሚናዎች እና ኃላፊነቶች

መመሪያው የተወሰኑ ወሳኝ የካፒታል ገበያ ተግባራት ፈቃድ ባለው ተሿሚ እንደራሴዎች ብቻ ሊከናወኑ እንደሚገባ ይደነግጋል።

ሀ) **ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች አስገዳጅ ተሿሚ እንደራሴዎች**:

መመሪያው ለተለያዩ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ዓይነቶች ሊኖራቸው ስለሚገባ ዝቅተኛ የተሿሚ እንደራሴዎች ቁጥር ይደነግጋል (አንቀጽ 15)። ከተለያዩ አይነት የሽርክና ማህበራት እና ከባለአንድ ሰው ኃ/የተ/የግል ማህበር በስተቀር ዋና የህግ ማስከበር መኮንን፣ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም ዋና ሥራ አስፈፃሚን ጨምሮ ሌሎች በባለስልጣኑ በየጊዜው የሚወሰኑ መደቦችን የሚይዙ ቢያንስ ሶስት ተሿሚ እንደራሴዎች ሊኖሯቸው እንደሚገባ መመሪያው ይደነግጋል።

ለ) **ተግባር ተኮር ተሿሚ እንደራሴዎች**:

ከእነዚህ ዋና ዋና ሚናዎች በተጨማሪ መመሪያው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ለልዩ ተግባራት ተሿሚ እንደራሴዎች እንዲኖራቸው ይጠይቃል:

- የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ እና አከናዋኝ በግብይት ፈጻሚነት ፈቃድ ያለው ተሿሚ እንደራሴ ሊኖረው ይገባል (አንቀጽ 41)።
- የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ኢንቨስትመንት አማካሪ በምርምር መኮንንነት ፈቃድ የተሰጠው ተሿሚ እንደራሴ ሊኖረው ይገባል (አንቀጽ 57)።
- የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንድ ሥራ አከናዋኝ በኢንቨስትመንት ሥራ አስኪያጅ ፈቃድ የተሰጠው ተሿሚ እንደራሴ ሊኖረው ይገባል (አንቀጽ 63)።
- የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገማች ድርጅት በገማች መኮንንነት ፈቃድ የተሰጠው ተሿሚ እንደራሴ ሊኖረው ይገባል (አንቀጽ 114)።
- የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ሮቦ-አማካሪዎች ዋና ሥራ አስኪያጁን እና ዋና የህግ ማስከበር መኮንኑን ጨምሮ በምርምር መኮንንነት እና በዋና ዲጂታል መኮንንነት ፈቃድ የተሰጠው ተሿሚ እንደራሴ ሊኖረው ይገባል (አንቀጽ 58)።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT

ይህ ስርዓት በካፒታል ገበያ የእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ወሳኝ ሥራ አስቀድሞ በተመረመረ፣ ብቃት ባለው እና ተጠያቂ በሆነ ባለሙያ እንደሚመራ ሥርዓት የሚዘረጋ ነው።

## 6. የተሿሚ እንደራሴዎች ስነ-ምግባር ደንብ፡

የመመሪያው ክፍል ሃያ ተሿሚ እንደራሴዎችን ጨምሮ ሁሉንም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጭዎች አጠቃላይ የስነ-ምግባር ደንብ ያቋቁማል። ይህ ደንብ የሙያቸው የስነ-ምግባር መሰረት ሲሆን ለሚፈጸሙ ጥፋቶች ተመጣጣኝ እና ከባድ ቅጣቶችም ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ተቀምጧል።

ተሿሚ እንደራሴዎች እና ሌሎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ሰራተኞች (አንቀጽ 161) የሚከተሉትን የስነ-ምግባር መርሆዎች እንዲያደርጉ ያስገድዳቸዋል፡

- ሁሉንም የካፒታል ገበያ እና ተዛማጅ ህጎች ማክበር፤
- ሐቀኛ መሆን እና የሙያውን ስም ከሚያጠለሽ ማንኛውም ድርጊት መታቀብ፤
- በሚሰጡት አገልግሎት ሁሉንም ያለአድሎ በእኩልነት ማስተናገድ፤
- ከተቀጣጣሪ ተቋማት ሰራተኞቻቸው፣ ከደንበኞቻቸው እና ከወደፊት ደንበኞቻቸው፣ ከሰራተኞቻቸው፣ከስፖንሰር አድራጊ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች እና ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ከፍተኛ ታማኝነት፣ብቃት፣ትጋት እና ሚስጢራዊነት ማሳየት
- ጥፋቶችን ለመለየት እና ለመፍታት መነጋገር
- የሙያ መስፈርቶች፣ ደንቦች እና ደረጃዎች አክብሮ መስራት (አንቀጽ 162)፤
- ጥፋቶችን እና የብቃት ማነስ ችግሮች ሲኖሩ ከሚመለከተው ሰው ወይም ሃላፊ ጋር በመነጋገር በመለየት በመተባበር መፍታት፣

**ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ፡-** ተሿሚ እንደራሴዎች ሙያዊ እውቀታቸውን በመጠበቅ ተገቢውን ክህሎት፣ ጥንቃቄ እና ትጋት ማሳየት አለባቸው።

**ሚዛናዊነት እና ተጨባጭነት፡-** ተሿሚ እንደራሴዎች ራሳቸውን ችለው መስራት እና ይህንን ተጨባጭነት የሚያጎድፍ ማንኛውንም ስጦታ ወይም ጥቅም መቀበል የለባቸውም።

**ታማኝነት እና ፍትሃዊነት፡-** ተሿሚ እንደራሴዎች ለደንበኞቻቸው ጥቅም ሲባል በሐቀኝነት መስራት አለባቸው፣ እንዲሁም የተሳሳተ መረጃ ለደንበኞቻቸው መስጠት የለባቸውም።

**የመጥፎ ባህሪ ክልከላ፡-** ተሿሚ እንደራሴዎች ከማጭበርበር፣ ወይም ከማታለል ጋር በተያያዙ ድርጊቶች ውስጥ መሳተፍ የለባቸውም።

እነዚህ አጠቃላይ መርሆዎች ለተለያዩ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ለምሳሌ፣ በአንቀጽ 170 ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላሎች፣ በአንቀጽ 172 ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የኢንቨስትመንት አማካሪዎች የየራሳቸው ተሿሚ እንደራሴዎች ተፈጻሚ ማድረግ የሚገባቸው የስነ-ምግባር ደንቦች አስቀምጧል።

## 7. ቀጣይነት ያላቸው ግዴታዎች እና ቀጣይነት ያለው ትምህርት

የተሿሚ እንደራሴዎች ቁጥጥር በፈቃድ አሰጣጥ አያበቃም፤ ይልቁንም በሙያቸው ጊዜ ሁሉ ቀጣይነት ያለው ሂደት ነው ።

**ሀ. ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ትምህርት**:

በመመሪያው አንቀጽ 127-130 መሰረት ተሿሚ እንደራሴዎች ጠንካራ ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ትምህርት ስርዓት እንዲኖር ያዛል። ሁሉም ተሿሚ እንደራሴዎች የሚከተሉትን መተግበር ይጠበቅባቸዋል፡-

- በእያንዳንዱ የፋይናንስ ዓመት ውስጥ ከስራቸው ጋር የሚዛመድ ቢያንስ አንድ ቀጣይነት ያለው

Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT

ሙያዊ ትምህርት ፕሮግራም ማጠናቀቅ አለባቸው (ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ትምህርት ዑደት)፤

- ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ትምህርት ፕሮግራሞቹ ለክህሎቶቻቸው፣ ለእውቀታቸው እና ለሥነ-ምግባር ደረጃዎቻቸው አስተዋፅዖ ማበርከታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፤
- ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ትምህርትን በባለሥልጣኑ እውቅና በተሰጣቸው ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ትምህርት ሰጪዎች ብቻ መውሰድ አለባቸው።

ስፖንሰር የሚያደርገው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ቀጣይነት ያለው ሙያዊ ትምህርት ፖሊሲዎችን የማቋቋም እና የተሿሚ እንደራሴዎች ተገዢነታቸውን የሚያረጋግጡ መዛግብትን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።

የቀጣይነት ያለው ሙያዊ ትምህርት መስፈርቶችን አለማሟላት በሠንጠረዥ ሶስት መሰረት ቅጣቶችን ያስከትላል።

**ለ. የአሰሪ ለውጥ መደረግ**

ተሿሚ እንደራሴ አሠሪዎችን ሲቀይር ባለሥልጣኑን ማሳወቅ አለበት። ተሿሚ እንደራሴዎች ስፖንሰር ሲቀይሩ በአዲሱ ስፖንሰር የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ስር መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል (አንቀጽ 125)። መመሪያው ተሿሚ እንደራሴዎች ቦታ ክፍት እንዲሆን አይፈቅድም። በአንጻሩ ማንኛውም ተሿሚ እንደራሴ ሥራ በሚለቅበት ጊዜ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪው ወዲያውኑ ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ሰው በመተካት ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት።

**ሐ. ዓመታዊ የፈቃድ እድሳት፡**

የተሿሚ እንደራሴዎች ፈቃድ በየዓመቱ በስፖንሰር አድራጊው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ የራሱን ፈቃድ ሲያድስ መታደስ አለበት (አንቀጽ 123)። ይህ የተሿሚ እንደራሴዎች ብቃት እና ተገቢነት በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዲቆይ ለማረጋገጥ ዓመታዊ የፍተሻ ነጥብ ይፈጥራል።

## 8. የተሿሚ እንደራሴዎች ፈቃድ ማገድ እና መሻር

መመሪያው ተሿሚ እንደራሴዎች ለህጉ ተገዢ ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የማስፈጸሚያ ሥርዓት ያቋቁማል። ባለሥልጣኑ በሚከተሉት ምክንያቶች የተሿሚ እንደራሴዎች ፈቃድን የማገድ ወይም የመሰረዝ ሥልጣን አለው (አንቀጽ 124)።

ፈቃድ ለማገዳ ወይም ለመሻር ምክንያቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ (አንቀጽ 124 እና 34):

- የስነ,ምግባር ደንቡን ወይም ሌሎች መመሪያዎችን አለማክበር፣
- የስፖንሰር አድራጊው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ፈቃድ ከታገደ ወይም ከተሰረዘ፣
- በባለሥልጣኑ ብቁ እና ተገቢ ሰው ሆኖ ካልተገኘ፣
- በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው በግል አቋሙ ግዴታውን የማይፈጽም ተብሎ ከተወሰነ፣
- ኪሳራ ከተወሰነበት፣
- ከሥነ-ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ በተፈጸመ ወንጀል ጥፋተኛ መሆን፤
- በውስጥ አዋቂ ንግድ ወይም በማጭበርበር ድርጊቶች መሳተፍ፣
- በጥያቄዎች ወይም በምርመራዎች ወቅት ከባለሥልጣኑ ጋር አለመተባበር፣እና
- ሌሎች በመመሪያው የተገለጹትን ከፈጸመ

የታገደ ፈቃድ ያለው ተሿሚ እንደራሴ በግብይት እና ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎች ላይ መሳተፍ አይችልም። በእገዳው ጊዜ ውስጥ ማንኛውም የካፒታል ገበያ እንቅስቃሴ በሥነ ምግባር ብልሹነት ምክንያት የሚመጣ መሻር አንድን ግለሰብ ውሳኔው ለካፒታል ገበያ አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ቀርቦበት ካልተሻረ

በስተቀር ለአዲስ ፈቃድ ብቁ እንዳይሆን ያደርገዋል (አንቀጽ 124(3))።